


# የፍጥረት አጀማመር [ዘፍ1$^{1}$-2$^{3}$]



እግዚአብሔር
የፍጥረታት
ፈጣሪ
ነዉ።



ከሰዉ በቀር
ሁሉንም የፈጠረዉ
በቃሉ
ነዉ።



ፍጥረቱን ካለመኖር ወደ
መኖር፤ ከምንም ነገር
ወደ አንድነገር፤
ከማይታይም ወደሚታይ
አምጥቷቸዋል።

“ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።” እንደሚል፡፡[ዕብ11[3]]



“መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥ለእኛስ ነገር ሁሉ <u>ከእርሱ የሆነ</u> እኛም <u>ለእርሱ የሆንን</u> አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም <u>በእርሱ በኩል የሆነ</u> እኛም <u>በእርሱ በኩል የሆንን</u> አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።”

[1ቆሮ8[5-6]]



“ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።”

[ዮሃ1[3]]



“ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው።” [ዕብ3[4]]

ተስለዚህም፣ በዚህ ዓለም የተደረጉ ግኝቶች ሁሉ አዲስ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞውንም ታዉቀዉ፥ የተሰሩ፥ የተሰወሩ፥ አልያም ከእግዚአብሔር ፍጥረት ሥርዓት የተኮረጁ (imitate የተደረጉ) እንደሆኑ እናያለን፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።


ምሳሌ፡-

- አዉሮፕላኖች ከወፎች፤
  - መርከቦች ከዓሶች፤
    - ሄሊኮፕተሮች ከበራሪ ፍጥረታት
      - ወዘተ ተኮርጀዋል።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።


እግዚአብሔር የጠለቀ ሚስጢሩን በፍጥረቱ አስቀምጧልና፤ የማይታየው የርሱ ባህርይ፥ የዘላለም ኃይሉ፥ ታላቅነቱ፥ አምላክነቱም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታዉቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል!![ሮሜ1[21]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።


…ያለመነም የጥበባት ሁሉ ምንጭ የሆነ እግዚአብሔር መኖሩን ከፍጥረት ይማራል!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## አንድም፤

ሰዉ እግዚአብሔር በፍጥረቱ የገለጠውንና የሰወረዉን ሚስጢር ማወቁ፤ ምን አይነት ድንቅ አምላክ እንደሆነ ከመረዳቱም ባለፈ የሚማረዉ እጅግ ድንቅ ትምህርትም አለ።



ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም አብዛኛው ትምህርቶቹን በምሳሌ አስደግፎ ማስተማሩ ፤ የተገለጡ ትንቢቶችም በራእዮችና በምሳሌዎች መሆናቸዉን፤ ላስተዋለዉ ሁሉ እግዚአብሔር የጠለቀ ሚስጢሩን በፍጥረት ሥራዓቱ እንዳደረገ ይገባዋል።





† ወደቀደመዉ ነገራችን እንመለስና፤ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ነበር ፤ ፍጥረትንም የፈጠረው እርሱ ነው፡፡ የፈጠረውም በኃይሉና በጥበቡ ከምንም ነው፡፡

† ፍጥረቱን በስድስት ቀን ፈጥሮ፣ በሰባተኛው ቀን በመፈጸም ከሥራዉ አርፏል፤ ቀኗንም ባርኳታል፥ ቀድሷታልም፤ የጀመረዉን ሥራ ጨርሶ ዐርፎባታልና!

† በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጥሯል፡፡[ዘፍ1[1]] በዚህም ልክ ማዕድናት መሬት ዉስጥ እንዳሉ ሁሉ፤ ሰማይ ሲል፥ በሰማይ ያሉትን መላእክትንና ያልተገለጡ ፍጥረቶችን ጨምሮ እንደሆነ እንረዳለን።